# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 11 መስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ሲዳሰስ



# የኢዜማ መልዕክት ለኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች

2012 የትምህርት ዘመን ተጀምሯል። የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ለመላው የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች መልካም የትምህርት ዘመን ይመኛል።

ኢትዮጵያ የወጣቶች ሀገር ናት፤ ዕጣ ፈንታዋ ያለው በወጣቶቿ መዳፍ ውስጥ ነው፤ ከወጣቶቿ በርከት ያሉት ደግሞ በትምህርት ገበታ ላይ ናቸው። ተማሪዎች በትምህርታቸው ወቅት የሚያደርጓቸው ተግባራት የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ብቻ ሳይሆን የአገራችንን ዕጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ኢትዮጵያዊ ወጣት ትምህርትን በትግል መሣሪያነት ሲጠቀም ቆይቷል። ከ1950ዎቹ ጀምሮ የተደረጉ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች የተጠነሰሱትና የተመሩት እድሜያቸው ከሀያዎቹ ባልዘለሉ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ ደረጃና በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ነበር። የሚያዝያ 30 ቀን 1997ን ታላቅ ሰልፍ ያደራጁ፤ ሕዝብን አደፋፍረው ለምርጫ በማሰለፍ ግንቦት 7 ቀን 1997 ታሪካዊ ዕለት እንድትሆን ያደረጉ፤ በኋላም የወላጆቻችንን ድምጽ አናስነጥቅም በማለት የታገሉ ወጣቶች ናቸው፤ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ነበሩ።

ባለፍት ሦስት ዓመታት በመላው ኢትዮጵያ የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ እምቢተኝነት ያደራጁ፣ የመሩና ኢትዮጵያ አገራችን አሁን በምትገኝበት የለውጥ ሂደት ውስጥ እንድትገባ ያደረጉ ወጣቶች ናቸው፤ ከእነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ በተለያዩ ደረጃዎች ይገኙ የነበሩ ተማሪዎች ናቸው፤ ከእነዚህ አብዛኛዎቹ ዘንድሮም ተማሪዎች ናቸው። ባለፉት ሶስት ዓመታት በሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ከተሳተፉ ተማሪዎች ውስጥ ብዙዎች ለጋ ሕይወታቸውን ሰውተዋል፤ ከዚያ በቁጥር በጣም የበዙት ደግሞ አካሎቻቸውን አጥተዋል። ባለፉት ሶስት ዓመታት ውስጥ ብቻ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሊያገኙ ይገባ የነበረውን የተሟላ ትምህርት ሳያገኙ ወደቀጣዩ ክፍል ተሸጋግረዋል፤ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ የዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጅ ተማሪዎች ከትምህርቶቻቸው ተሰናክለዋል። በርካታ የትምህርት ቀናት ለሕዝባዊ እምቢተኝነት ውለዋል። ይህ ሁሉ ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለሀገር አንድነትና ለብሔራዊ ክብር የተከፈለ መስዋዕትነት ነው።

ዛሬ የምንገኝበት ፓለቲካዊ ድባብ አገራችን ከዚህ በፊት ከነበረችበት የተለየ ነው። ብዙ ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎች ቢኖሩ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መጠየቅ የምንችልበት ሥርዓት እየተዘረጋ ነው። ጊዜው ሲቀየር የትግል ስልት መቀየር ይኖርበታል። የትግል ስልት ሲቀየር የዕለት ተዕለት ተግባሮቻችን ጭምር ይቀየራሉ።

በዚህም መሠረት ዛሬ የምንገኝበት ነባራዊ ሃቅ ከመናገር ይልቅ መስማት፤ ከአመጽ ይልቅ ትብብር፤ ከጉልበት ይልቅ ብልሃት፤ ከግልፍተኝነት ይልቅ እርጋታ፤ ከቀስቃሽ መፈክሮች ይልቅ የተብራሩ ሀሳቦች፤ ከችኩል ውሳኔዎች ይልቅ ማስተዋል የሚመረጥበት ወቅት ነው። ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ይህን ለውጥ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኢዜማ ያሳስባል። ኢዜማ በአገራችን እንዲመጣ የምንፈልገውን ለውጥ በየራሳችን ተግባራት መቀየር ማየት መጀመር አለብን ይላል። የአገራችን ፓለቲካ ከኃይል ይልቅ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ኢዜማ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል።

የትግል ስልት መቀየር ማለት በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ቅራኔዎች ግዴለሽ መሆን ማለት አይደለም። ወጣቶችና ተማሪዎች በየአካባቢያቸው ያሉትን ቅራኔዎችን ቸል ማለት እንደማይቻላቸው ኢዜማ ይገነዘባል። ተማሪዎች ለየአካባቢያቸው ከዚያም አልፎ ለሀገራዊና አህጉራዊ ችግሮች ትኩረት መስጠታቸው ተገቢ ነው። እንዲቀየር የሚፈለገው "የቅራኔዎች አያያዝና እና መፍትሔዎቻቸው" ነው።

አሁን ያለውን ፓለቲካዊ ድባብ ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ የቱን ያህል የተወሳሰቡ ቢመስሉም አገራችን የገጠሟትን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ መፍታት ይቻላል ብሎ ኢዜማ ያምናል፤ ይህ እምነት እውነት እንዲሆን ግን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት (በተለይም ተማሪው) የዚህ እምነት ተጋሪ ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያን ተማሪዎች በታደሰ መንፈስ ከጎናችን የሚቆሙ ለሆነ በአገራችን ያሉ ቅራኔዎችና ችግሮች ወደ እድገትና ትብብር እንጂ ወደ ውድቀትና የእርስ በእርስ ግጭቶች እንዳያመሩ ቅራኔዎችን የመግራት ጥበብ ማዳበር እንችላለን። ይህን ቅራኔዎችን የመግራት ጥበብ ከዘንድሮው 2012 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በሁሉም የትምህርት ተቋማት ተግባዊ ሲሆን እናያለን ብሎ ኢዜማ ተስፋ ያደርጋል።

በ2012 የኢትዮጵያ ተማሪዎች አገራችን የምትገኝበትን ልዩ ወቅት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎቻቸውን በመከባበር፣ በመተባበር እና በመደማመጥ ይቃኛሉ ብሎ ኢዜማ ተስፋ ያደርጋል።

2012 የትምህርት ዘመን ቅራኔዎች የዕድገት ምንጭ እንጂ የግጭቶች ምንጭ የማይሆኑበት ዓመት እንዲሆን ኢዜማ ይመኛል። የ2012 የትምህርት ዘመን የትምህርት ተቋሞቻችን ዕውቀት የሚገበይባቸው፤ ማኅበረሰባዊ ትስስር የሚዳብርባቸው፤ ተስፋ የሚለመልባቸው፤ ቅራኔዎች የዕድገትና የአዳዲስ ሀሳቦች ምንጭ እንዲሆኑ ይመኛል።

**መልካም የትምህርት ዘመን**

# ለኢዜማ ዓለም ዓቀፍ ድጋፍ ማኅበር ምስረታ የከተማ ምርጫዎ ተጀመሩ

መስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ዓለምዓቀፍ ድጋፍ ማኅበር በሰሜን አሜሪካ ሲያትል ከተማ ምርጫ ማካሄዱን የኢዜማ ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ምርጫው በሀገረ አሜሪካ በሲያትል ከተማ መስከረም 10 ቀን 2012 ዓ.ም የተካሄደ መሆኑንና በሚቀጥለው ሳምንትም በዋሽንግተን ዲሲ ተመሳሳይ ምርጫ እንደሚካሄድ እንደሚካሄድ የዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪው ጠቁመዋል፡፡

ሲያትል በተደረገው ምርጫ ነጋ አባተ የከተማው የኢዜማ ድጋፍ ማኅበር ሊቀመንበር ሆነው የተመረጡ ሲሆን ሰይፉ ኃይለሚካኤል የአባላት ጉዳይ ኃላፊ፣ ፈቃደ ተሰማ የሕዝብ ግንኙነት፣ እንዳለ አንዲኖ የከተማ ፖሊሲ ጉዳይ ኃላፊ እዲሁም ቢኒያም ደሜ ገንዘብ ያዥ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ የሲያትል ከተማ ድጋፍ ማኅበርን በመወከል ለክፍለ ዓለም እና ዓለምአቀፍ ኮሚቴዎች አመራርነት ደግሞ መቅደስ ተለለ እና ሰለሞን ተስፋዬ መመረጣቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የኢዜማ ዓለምዓቀፍ የድጋፍ ማኅበር በሀገር ውስጥ ፓርቲው በተቋቋመበት መንገድ ከከተማዎች ጀምሮ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በአባላት በሚመረጡ አስተባባሪዎች የሚመራ ሲሆን በክፍለዓለም እና በዓለምዓቀፍ ደረጃም አስተዳዳሪዎች ምርጫ እንደሚካሄድ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ ላይ ምርጫዎች የሚካሄዱ ይሆናል፡፡

ኢዜማ ባሳለፍነው ሳንት አርብ መስከረም 9 ቀን 2012 ዓ.ም ‹‹ለኢትዮጵያ ተስፋ ከኢዜማ ጋር በጋራ እንሥራ›› በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ የዓለምዓቀፍ ድጋፍ ማኅበሩ ከ70 በላይ በሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው ከተሞች ምርጫ ለማካሄድ እየሠራ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡ ፓርቲው በመግለጫው በውጪ የሚኖሩ ከዚህ በፊት በተለያየ መንገድ የፖለቲካ ተሳትፎ ያደረጉ እ የፖለቲካ ተሳትፎ መጀመር ለሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በየሚኖሩበት ከተማ በሚመሰርቱት የድጋፍ ማኅበራት አባል በመሆን ለሀገራቸው የበኩላቸውን እንዲያደርጉና ከኢዜማ ጋር በጋራ እንዲሠሩም ጥሪውን አስተላልፏል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

መስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ሲዳሰስ

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የመጀመሪያው የፖሊሲ አቅጣጫ መድረክ ነሐሴ 27 እና 28 ቀን 2011 ዓ.ም መካሄዱ ይታወቃል፡፡ በዚህ መድረክ ላይ ከቀረቡት ጥናቶች መሀከል አንዱ የትምህርት ፖሊሲ ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ አንዱ ዓላማ የትምህርት ፋይዳን ማስገንዘብ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት መውደቅ (የትምህርት ቀውስ) ዋና ምክንያት የኢህአዴግ መንግሥት በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የሚያደርገው ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ከዚህም ተከትሎ የመጣው የአካዳሚ (የመማር እና የማስተማር) ነጻነት መጥፋት ያመጣውን ችግር ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ጥራትና አግባብነት ያለው የትምህር ሥርዓት ለመዘርጋት በትምህርት ተቋማት ነጻ አካሄድ መኖር እንዳለበት ይሞግታል፡፡ በዚህ ጽሑፍ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ያለበትን ችግሮች በአጭሩ በመዘርዘር መሠረታዊ ለውጥ እንደሚሻ ይጠቁማል፡፡

ከትምህርት ሥርዓቱ ጋር በተያያዘ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ስለትምህርት እና በተለይም የትምህርት ሥርዓቱ ያለበትን ሁኔታ በመንግሥት ኃላፊዎች በተላለፉ ውሳኔዎች ላይ በመገናኛ ብዙኃን መግለጫ መስጠቱ ይታወሳል፡፡ በአጠቃላይ የሕዝብን ትኩረት የሳቡ ሀገራዊ ጉዳዮች በመሆናቸው መፍትሔ በማፈላለግ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን የተሰጡት መግለጫዎች ላይ አስተያየት መሰንዘር የዚህች ዳሰሳ ጽሁፍ ሌላው ዓላማ ነው፡፡

በአጠቃላይ ወደፊት የሚጠበቀው የትምህርት ሥርዓት ለውጥ በትክክልና በተሻለ ፍጥነት እንዲጓዝ ለማድረግ የትምህርት ማኅበረሰቡ ሙሉ ተሳትፎ የሚጠይቅ ሀገራዊ ጉዳይ በመሆኑ ሁሉም እንዲሳተፍ ለማሳሰብ በማሰብ የተዘጋጀ ጽሑፍ ነው፡፡

## 2. የትምህርት ዓላማና ፋይዳው

ትምህርት የአጭርም፣ የረጅምም ጊዜ ሂደት ሆኖ ህብረተሰቡ ያከማቸውን ዕውቀት ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ፣ የአሁኑን ዕውቀት ደግሞ ለማጎናጸፍ እና አዲስ ዕውቀትም ለማመንጨት የሚደረግ ማኅበራዊ ተግባር ነው፡፡

የትምህርት ዋና ግብ ለሀገር ዕድገት እና ዴሞክራሲ የቆመ፣ ጥልቅ ዕውቀት ያለው፣ ብሩህ ተስፋ የሰነቀ፣ ችግር ፈቺ ትውልድ ማፍራት ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነች ኢትዮጵያን ለመገንባት ትምህርት ቁልፍ የኾነ ሚና አለው፡፡ ከዚህም በላይ ዜጎች የሚኖሩበትን ማኅበረሰብ ለማገልገል የሚያስችላቸውን የተሟላ ስብዕና በማላበስና ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ትምህርት ለሀገር ዕድገት እና ብልጽግና ምሰሶ መሆኑን ኢዜማ በጥልቀት ያምናል፡፡ ስለሆነም ኢዜማ ጥራቱን እና አግባብነቱን የጠበቀ ትምህርት በመላው ሀገራችን ለማዳረስ ግልጽ ዓላማ እና ቁርጠኛ አቋም ይዞ የሚጓዝ ሀገራዊ ፓርቲ ነው፡፡ ስለዚህም፣ ኢዜማ ለሚያቅዳቸው እና ለሚተገብራቸው ዘርፈ ብዙ የልማት ውጥኖች መሠረታዊ ግብዓቶች የሆኑትን በክህሎት ብቁና፣ ሥነ ምግባራዊ ልዕልናው የላቀ የሰው ኃይል ለማዘጋጀት የትምህርት ፖሊሲ አማራጭ ሀሳብ በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡

## 3. የትምህርት ሥርዓቱ ችግሮች

አሁን የትምህርት ሥርዓቱ ላይ ያሉበት ዋና ዋና ችግሮች የተፈጠሩት በኢህአዴግ መንግሥት ጣልቃ ገብነት መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም፡፡ የዛሬ 27 ዓመታት አካባቢ 42 አንጋፋ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራንን በማባረር መንግሥት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት አይኑን ያፈጠጠ ጣልቃ ገብነቱን በግልጽ ሲያሳይ ነው፡፡ የተባረሩት መምህራን ላይ የደረሰው ኢ- ፍትሃዊ እርምጃ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በፍርሃት ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲነግስ አድርጓል፡፡

ከመባረር የተረፉት መምህራን አንድም በፍርሃት እየኖሩ እንዲያስተምሩ፣ አለበለዚም ተቋሙን እየለቀቁ እንዲሄዱ ምክንያት ሆኗል፡፡ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር በመፍረሱ ምክንያት መምህራን የሙያ ግዴታቸውን በትክክል ለመወያየት እና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚደርሱ ችግሮችን ለመፍታት የሚመካከሩበት መድረክ ነጠፈ፡፡ ይህ ሁኔታ ለትምህርት ጥራት መውደቅ አስተዋጽዖ ማድረጉ ግልጽ ነው፡፡

ሌላው የትምህርት ሥርዓቱን ውድቀት ላይ የጣለው ጣልቃ ገብነት የተቋማት አመራሮች አመራረጥ እና ሹመት በመንግሥት ፖለቲካ ታማኝነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው፡፡ የተቋማት አመራሮች ማለትም ፕሬዝዳንቶች፣ የተቋማት ዳይሬክተሮች፣ የተቋማት ዋና አስተዳዳሪዎች፣ ርዕሰ መምህራን ወዘተ ሁሉ ኃላፊነት የሚቀበሉት ከበላይ አካል/ ከባለሥልጣን ነው፡፡ ስለሆነም የእነዚህ ግለሰቦች ሙሉ ትኩረት መመሪያ/ትዕዛዝ ተቀብሎ መፈጸም/ማስፈጸም ብቻ ነው፡፡

ይህ ዓይነት ኃላፊነት ያገኘ ተጠያቂነትን ከሚያገለግለው ማኅበረሰብ ጋር የሚያገናኝ ሳይሆን፣ ኃላፊነቱን ለሰጠው ባለሥልጣን ታዛዥነትን የሚያጠናክር ነው፡፡ ለዚህ ነው የትምህርት ተቋማቱ ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታዎችና ያለባቸውን ውድቀት መምህራን፣ ተማሪዎች ወላጆች እና ቀጣሪ ድርጅቶች በትክክል የማያውቁት፡፡ ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ሊቀጥል አይገባም፡፡ ይህን በመገንዘብ ይመስላል፤ ከቅርብ ወራት ወዲህ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፖለቲካው ውጭ የሆኑ ግለሰቦች በቦርድ አባላት እንዲሠሩ መፈቀዱ፡፡ ይህ አካሄድ ለሚጠበቀው ለውጥ ጭላንጭል ቢሆንም ከላይ ወደታች የሚታቀድ አካሄድ ምን ያህል ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል በሂደት የሚታይ ይሆናል፡፡

የፖለቲካው ጣልቃ ገብነት "አውቅልሃለው" ዓይነት በሚል ፈሊጥ ከላይ ወደታች በተቀመጠ ተዋረድ በየትምህርት ዘርፉ (ለምሳሌ የታሪክ ትምህርት) ባሉ ክፍሎች ሙያዊ ሥራ ውስጥ እየገባ የትምህርቱ ማኅበረሰብን (መምህራን፣ተማሪዎችንና ተቋሙን) ድምጽ-አልባ በማድረጉ አሁን ላለንበት የትምህርት መውደቅ ቀውስ እንድንዳረግ አድርጎናል፡፡ ይህ በመሆኑም ከትምህርት ማኅበረሰቡ ሊመነጭ የሚችለውን አዳዲስ ጠቃሚ ሀሳቦች፣ የአሠራር ዘይቤዎች የጥናት፣ ምርምር እና ውጤቶች ለትምህርት ሥርዓቱ ተገቢውን አስተዋጽዖ ሊያደርጉ

ባለመቻላቸው የመጣ ችግር ነው፡፡

የትምህርት ሥርዓቱ ችግር ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ችግሮች ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ (የዩኒቨርሲቲ መግቢያ) ፈተና ጉዳይ ባፉት ዓመታት የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥሙት እንደነበር የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ዓመትም በፈተና ውጤት ዙሪያ ችግር እንዳጋጠመ በተከታታይ በመገናኛ በሚያመለክት መንገድ ሁኔታውን ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት፡፡ ለችግሩ መፍትሔ ለመሻትና እነዚህ ችግሮች ወደፊት እንዳይቀጥሉ ለማድረግ ኤጀንሲውና የሚመለከታቸው ግለሰቦች በሕግ እንዲጠየቁ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

አንድ መሠረታዊ እና ብዙም የማንነጋገርበት ጉዳይ በዚህ አጋጣሚ መጥቀስ ይገባል፡፡ ይኸውም ወደ ዩኒቨርሲቲዎች የመንግሥት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የዘረጋው ጣልቃ ገብነት መሆኑን አለመግለጹ አሁንም መንግሥት የችግሩን ዋና መንስዔን አምኖ አለመቀበሉን ያመለክታል፡፡ የ8ኛ፣ የ10ኛ እና የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ወደ 6ኛ፣ 8ኛ እና 12ኛ መቀየር እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርትን ከ3 ዓመት ወደ 4 ዓመት መለወጥ የትምህርት አደረጃጀት እና አመራር ዘይቤ

# ‹‹የትምህርት ጥራት አግባብነት መውደቅ ከሌሎች ሁሉ የላቀው ችግር እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡››

ብዙኃን ዘዴዎች ሲነገር ቆይቷል፡፡ በመጨረሻም ሁሉንም ግራ የሚያጋባ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ይኸውም በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች የፈተና ውጤቱ የጋሸበ በመሆኑ፣ የእነዚህ ትምህርት ዓይነቶች የፈተና ውጤት ውድቅ ተደርጎ አስተማማኝ ውጤት የተገኘባቸው በተባሉ 4 የትምህርት ዓይነቶች ውጤት ብቻ ተወስኗል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ምደባም በዚሁ የሚከናወን መሆኑ ተነግሮ የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርም የዩኒቨርስቲ መግቢያ ነጥቡን በቅርቡ ይፋ አድርጓል፡፡

ይፋ የሆነው የፈተና ውጤት ችግር እዴት ሊከሰት እና ተያይዞም የውጤት መጋሸብ ሊያስከትል እንደቻለ በግልጽ የታወቀ ነገር የለም፡፡ ለችግሩ ተጠያቂው አካል፣ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤትም ይሁን ግለሰብ (ግለሰቦች) ማን እንደሆነ የተሰጠ መረጃ የለም፡፡ ስለዚህም ችግሩን ለመፍታትም ሆነ ወደፊት ሊደረጉ ስለሚገባቸው የእርምት እርምጃ ዓይነቶች አስተያየት መስጠት ያስቸግራል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ተፈታኝ ተማሪዎች፣ ወላጆች እና መምህራን በትምህርት ሥርዓቱ ላይ መተማመን እንዳይኖራቸው፣ በፍትሃዊነቱ ላይም ጥያቄ እንዲያነሱ የሚያደርግ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በሕዝብ ዘንድ የተከሰተው ከፍተኛ ቅሬታም ችግር ውስጥ ለሚገኘው የትምህርት ሥርዓት የበለጠ ማጥ ውስጥ የሚያስገባ ግዙፍ ችግር ነው፡፡ ስለዚህም የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተለይም የብሔራዊ ፈተናዎች ኤጀንሲ ግልጽነት በተሞላበት እና ተጠያቂነትን የሚገቡ ተማሪዎች በፍላጎት እና በችሎታ ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ሊኖር ሲገባው ተማሪዎች የሚፈልጉትን የትምህርት ዓይነት እንዲማሩ ማድረግ አለመቻል አንዱ የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ችግር ነው፡፡ የማትፈልገውን የትምህርት ዘርፍ በማትፈልገው ዩኒቨርሲቲ ገብታ እንድትከታተል የተደረገች (የተገደደች) ተማሪ ምን ያህል አጥጋቢ ውጤት ልታስመዘግብ ትችላለች? ይህ የሁላችንም ጥያቄ ሊሆን ይገባል፡፡

የትምህርት ጥራት አግባብነት መውደቅ ከሌሎች ሁሉ የላቀው ችግር እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ ታዲያ ለዚህ ኃላፊነት የሚወስደው መንግሥታዊ ተቋም፣ የከፍተኛ ትምርት ጥራት እና አግባብነት ኤጀንሲ ነው፡፡ ይህ ኤጀንሲ የሚያደርገው ጥናት፣ ክትትል እና የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓት መኖሩ በጉልህ አይታይም፡፡ ከኤጀንሲው የምንሰማው የግል ኮሌጆች አና ዩኒቨርሲቲዎች ዕውቅና ሲሰጥ እና የዕውቅናውም ዜና በመገናኛ ብዙኃን ሲነገር ነው፡፡ ሌላውን ኃላፊነት እንዴት እንደሚወጣው ግልጽ መረጃ የለም፡፡

ሌላው ወቅታዊ ጉዳይ፣ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት በትምህርት ሚኒስቴር፣ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ባለሥልጣናት በችግሮቹ ዙሪያ መፍትሄ ለመሻት በማለም በተዘጋጀው የትምህርት ፍኖተ ካርታ ላይ ተከታታይ መግለጫዎች ሰጥተዋል፡፡ ምንም እንኳን የዘገየና ውስንም ቢሆን ችግሮችን ሕዝብ እንዲያውቃቸው መደረጉ የሚደገፍ ነው፡፡ ሆኖም የትምህርት ሥርዓቱ ዋና ችግር ሳይለወጥ ምን ያህል ለውጥ ሊያመጣ ይችል ይሆን? የሚል ጥያቄን ያጭራል፡፡

የኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት ችግር የሚጀምው ከ1ኛ ደረጃ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ነው፡፡ የመጀመሪያው የትምህርት ዘመን ለታዳጊ ህጻናት ማኅበራዊ ጥበብን፣ ስለራ ማወቅን፣ ግብረ-ገብነትን ለመቀበል ምቹ የሆነ ሰፊ የማወቅ ፍላጎትን የሚያስተናግዱበት የብሩህ አዕምሮ ጊዜ ነው፡፡

ይህ የመጀመሪያ የመማሪያ ዘመን ሕጻናት ከቤተሰቦቻቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ተለይተው ትምህርት ቤቱን መልመድ፣ ከሌሎች ልጆች ጋር መዋልና መጫወት፣ ከመምህሩ ጋር መግባባት የሚጀምሩበት ሲሆን ትምህርታቸውም በጨዋታ እና በእንቅስቃሴ እንዲሁም በተረት ላይ ያተኮሩ እና በደማቅ ቀለማት ባሸበረቁ ክፍሎችና ንጹህ ጊቢ መካሄድ እንዳለበት ተመራማሪዎች በግልጽ ይመክራሉ፡፡ ከዚህም በላይ ለደረጃው ልዩ ብቃት ያላቸው መምህራን ሊሰለጥኑ ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይህ ትኩረት ስለማይታይ የትምህርት ጥራት ውድቀት የሚጀምረው እዚህ ላይ ነው፡፡ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚታየው ድክመት ምክንያት ወላጆች ልጆቻቸውን በግል ትምህርት ቤቶች ለማስተማር ሲፍጨረጨሩ ይታያል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፍትሃዊ እና የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓቱ ብርታት የሚሆነው የ1ኛ ደረጃ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን ማጠናከር ሲቻል ነው፡፡

ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት ጋር በተዛመደ

በሰሞኑ የመንግሥት ፍኖተ ካርታ ዙሪያ ከተነሱ ዋና ጉዳዮች አንዱ የማተማሪያ ቋንቋ ነው፡፡ ማንኛውም ትምርት እና ሥልጠና የሚሰጠው በቋንቋ አማካኝነት ነው፡፡ ቋንቋ ዕውቀት ለመገብየት ዋናውና ተቀዳሚ መንገድ ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ሀገር ናት፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ብዙ ቋንቋ የአፍሪካ እና እስያ ሀገሮች የማስተማሪያ ቋንቋ ጉዳይ ለረጅም የሚጠይቀውን መሠረታዊ ክንዋኔዎች (በቋንቋው የሰለጠነ መምህር፣ የቋንቋው ፊደል፣ የንባብ መጸሐፍ ወዘተ...) በትክክል እና በአግባቡ ባለመዘጋጀታቸው የማስተማሪያ ቋንቋ ችግር ለትምህርት ጥራት መውደቅ አንዱ ምክንያት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለወደፊት ግን በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር እንዲቻል የሚስፈልጉ ግብዓቶችን አንድ በአንድ እየተጠና እና እየተመረመረ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን በዩኒቨርስቲዎቻችን ውስጥ ሊዘወተሩ ይገባል፡ ፡ ስለዚህ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መተዋወቅ እንዲችሉ ለዓላማ እና ለግባቸው እንዲሠሩ ሁኔታችን ማመቻቸት የእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል፡፡ ከ2011 ዓ.ም ሁኔታ በመማር ሰላማዊ የመማር - ማስተማር ሂደት በሁሉም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲኖር ማድረግ ለከፍተኛ ትምህርት ጥራት ወሳኝ ነው፡፡

**‹‹አማርኛ የፌደራል መንግሥት አፌሴላዊ የሥራ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ የንግድ እና የመግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት መሰጠት አለበት፡፡››**

ጊዜ ብዙ ጥናትና ምርምር ተካሂዶ በዩኔስኮም ቁርጠኛ አቋም የተወሰደበት መስክ ነው፡፡

ለጀማሪ ሕጻናት ትምህርት በአፍ መፍቻ (የእናት) ቋንቋ መማር ትምህርቱን በቀላሉና በፍጥነት እንዲቀበሉ፣ ትምህርት ቤቱንም እንዲወዱ እንደሚያደርግ ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአፍ መፍቻ (እናት) ቋንቋ መማር ከትምህርት ቤት የተገኘ ዕውቀት ከብሔረሰቡ ባሕልና ልምድ ጋር ማዛመድ ስለሚያስችል፣ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ወሳኝ የሆነውን የትምህርት ቤት፣ ተማሪ እና ወላጆች አብሮ መሥራትን ያበረታታል፡፡

አማርኛ የፌደራል መንግሥት አፌሴላዊ የሥራ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ የንግድ እና የመግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት መሰጠት አለበት፡፡ የሀገሪቱን (የፌደራል መንግሥቱን) የሥራ ቋንቋ ጠንቅቆ ማወቅ ለሀገራዊ አንድነት እና ወጣቶች በሀገሪቱ ሁሉም ክፍሎች (ክልሎች) ተዘዋውሮ ለመሥራት በማስቻል ሥራ የማግኘት ዕድል በማስፋት የተማረው ወጣት ለሀገሩ የሚፈለግበትን አስተዋጽዖ እንዲያከናውን ይረዳል፡፡

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት መጨረሻ ድረስ የማስተማሪያ ቋንቋ በመሆኑ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ በጥልቀት እንዲሰጥ ማድረግ የተማሪዎችን ቀጣይ ትምህርት የተሳካ እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸው እንዲዳብር ያደርገዋል፡፡

የኢህአዴግ የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ (1986 ዓ.ም) የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በብሔር/ብሔረሰብ ቋንቋ እንዲካሄድ ቢደነግግም፣ ለማስተማሪያነት ማብቃት ለማስተማሪያ ቋንቋነት ብቃት እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 4. የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ መምህራን እና ‹‹የካምፓስ ባሕል››

በ2011 ዓ.ም የሰማነው እና የተገነዘብነው በተማሪዎች መካከል ሲንጸባረቅ የነበረው ግጭት ከዘውግ ተኮር የኢህአዴግ የፖለቲካ አመለካከት የመነጨ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች አዕምሮና አስተሳሰብ ላይ ያመጣው ችግር ነው፡፡

ስለዚህ በ2011 ዓ.ም የትምህርት ዓመት የመማር - ማስተማር ሂደት የነበረው አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳይደገምና ወደፊት በሰላም እና በተሳካ ሁኔታ ይካሄድ ዘንድ መንግሥት (የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር) የተጣለበትን ኃላፊነት በትክክል ሊወጣ ይገባል፡፡ ተማሪውም በማንነት ላይ የተመሠረተ ከፋፋይ የፖለቲካ አስተሳሰብ በቀላሉ ነጻ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር እና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከተለያየ ባሕል እና አካባቢ የመጡ ተማሪዎች በአንድ ጊዜ፣ በተመሳሳይ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ቆይታ ሲያደርጉ ሊከተሉት የሚገባው በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መወያየትን እና መመካከር የሚያበረታታ፣ የዴሞክራሲ እሴቶችን የሚያከብር፣ የማንነት ተኮር ግጭት የሚያስወግድ "የካምፓስ ባሕል" መፈጠር እና መዳበር አለበት፡፡ በሀገራችን ዩኒቨርስቲዎች ጊቢ ውስጥ የቋንቋ፣ የባሕል፣ የሃይማኖት ወ.ዘ.ተ.... ብዝኃነትን የምናየው ሲሆን ለሀገራችን አንድነት እና ለጠንካራ የእርስ በርስ መስተጋብር የሚበጁ ውይይቶች

በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን የሚመለከት አንድ ትንሽ ጥያቄ ማንሳት ግድ ይላል፡፡ በዩኒቨርሲቲ ጊቢዎች ተፈጥሮ የቆየውን ችግር በመፍታት ረገድ የዩኒቨርሲቲ መምህራን የሞራል ግዴታ ተወጥተዋል ወይ? በእርግጥም የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ኃላፊነት ማስተማር፣ ምርምር ማካሄድ እና ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ መምህራን ከሚያስተምሩት ትምህርት ውጪ በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ በተማሪዎች መካከል የሚከሰቱ ችግሮችንና ግጭቶችን በመፍታት ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ መምህራን ሙያቸውን በሚመለከት ጉዳይ ላይ በሥራ በተለይም በትምህርት ይዘት እና አግባብነት መውረድ ዙሪያ ምክክር ለማድረግ የሚያስችል የጋራ መድረክ እንኳን የላቸውም፡፡ መምህራን በራሳቸው የመመካከሪያ መድረክ መፍጠር ለአጠቃላይ የትምህርት ሥርዓቱ ለውጥና ለሙያቸው መዳበር ቁልፍ መሆኑን ኢዜማ በጥልቅ ያምናል፡፡

## 5. የትምህርት ትኩረት አቅጣጫችን

ያለንበት የትምህርት ሥርዓት ላይ በተጠቀሱት ድክመቶች ዙሪያ በመነሳት የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ለውጥ አስፈላጊነት ብዙም የሚያነጋግር አይደለም፡ ፡ የኢህአዴግ መንግሥት በገጠርም በከተማም ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት፣ ዩኒቨርሲቲዎችን ቁጥር 44 በማድረስ፣ ብዛት ያላቸው የቴክኒክና ሙያ እንዲሁም የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማትን ለማቋቋም የተደረገው

ጥረት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የለውጡ መንገድ ምን መምሰል አለበት? ትኩረታችንስ ምን ላይ ሊሆን ይገባል የሚለውን ለመዳሰስ አስፈላጊ ነው፡፡

ኢዜማ የትምህርት ሥርዓቱ የገባበት ውስብስብ ችግር በተለይም የትምህርት ጥራትና አግባብነት መውደቅ መሠረታዊ ለውጥ የሚፈልግ መሆኑን ይገነዘባል፡፡ ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነጻ የሆነ፣ ተማሪ ተኮር፣ መምህሩን ማዕከል ያደረገ፣ የትምህርት ማኅበረሰቡን የሚያሳትፍ አደረጃጀትና አመራር የሚኖረው ዘላቂ ሥርዓት መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ በተሟላ የመማር - ማስተማር ሂደት፣ ብቃትና ተነሳሽነት ባላቸው መምህራን፣ የአካዳሚ ነጻነት በተከበረበት ግቢ፣ ጥራትና አግባብነት ያለው፣ ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ትምህርት በፍትሃዊነት የማዳረስ አቅጣጫ ነው፡፡ ስለዚህም የትምህርት ሥርዓቱን ከታች ወደ ላይ (ከ1ኛ ክፍል እስከ ድኅረ ምረቃ ፕሮግራሞችን) በጥልቅ በመመርመርና ሰፊ ምክክር ለማካሄድ እንዲቻል 10 የትኩረት ነጥቦችና አቅጣጫዎች በአጭሩ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

1. የ1ኛ ደረጃ በተለይም የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትና ወላጆች (የወላጅ ኮሚቴ) ተሳትፎ እዲኖር በማድረግ የማንኛውም ተማሪ የወደፊት ትምህርት አቀባበልን የተሳካ ስለሚያደርግ ከመጀመሪያው ትኩረት ይሻል፡፡
2. ባሕላዊ እና ሀገር በቀል ዕውቀትን በትምህርት ካሪኩለም ተገቢውን ቦታ የሚሰጥ ሥርዓት ጥቅሙ ሰፊ ነው፡፡ በሀገራችን በባሕል፣ በቋንቋ፣ በመልክአ ምድር፣ በአኗኗር ዘይቤ ሊገኝ የሚችለውን ሀገር በቀል ዕውቀትን መማር የባሕል ትስስርን ከመፍጠሩም በላይ ለሀገር አንድነት ጥቅሙ የጎላ ነው፡፡
3. የመማር - ማስተማር ግብዓቶችን ከ1ኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ድሕረ ምረቃ ፕሮግራም ድረስ በጥምና መመረመር እና ማቀናጀት ጥራትና አግባብነት ላለው ትምህርት መሠረት ነው፡፡
4. የሀገራችን ትምህርት ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ዛሬ ዓለም በብዙ መንገድ በተገናኘበትና አብሮ በሚሠራበት ዘመን የትምህርት ጥራቱ በብሔራ ፊተናና በተቋማት መመዘኛ ብቻ የሚወሰን ሊሆን አይገባም፡፡ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነቱን ለማስመስከር እንዲቻል የሌሎች ሀገሮችን መመዘኛ በመጠቀም ማወዳደር ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ በሂሳብ ትምህርት የኢትዮጵያ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ከደቡብ ኮሪያ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር ማወዳደር ይቻላል፡፡ ጥራትና አግባብነት ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ያገኘ ወጣት ለሀገሩ ሥራ ፈጣሪ በተቀረው ዓለምም ተወዳዳሪ ያደርገዋል፡፡
5. የትምህርት ተቋማት አመራሮች ብቃት፣ ልምድና የአመራር ብስለት ያላቸው ባለሙያዎች እንዲሆኑ መምህራንና ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው "የእኔ ነው!" ብለው እንዲቀበሉ በተቋሞች ውሳኔ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሊያደርጉም ይገባል፡፡ ስለዚህም በልምድ፣ በብቃት እና ተፈላጊነት የተመሠረተ፣ መምህራን እና ተማሪዎች በሚሳተፉበት የሚመለመል ተጠያቂነቱም ለተማሪው፣ ለመምህራንና ለወላጆች የሆነ አመራርና አደረጃጀት ሊመሠረት ይገባል፡፡
6. መምህራን ለትምህርት ሥርዓቱ ቁልፍ በመሆናቸው የሥራ ተነሳሽነታቸውን የተፈታተኑትን ምክንያቶች በማጥናትና መወያየት የማሻሻል እርምጃዎ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት ያላቸው መምህራን እጥረትን ለመቀነስ በውጭ ሀገራት የሚያስተምሩ ኢዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን እንዲሳተፉ በማድረግ እንዲሁም የቀድሞ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች (ለምሳሌ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ማኅበራት እንዲመሠርቱ በማድረግ መፍትሔ ሊገኝ ይችላል፡፡
7. የትምህርት አገልግሎት በሴት እና በወንድ ተማሪዎች እንዲሁም በገጠር እና ከተማ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ እና ከትምህርት ገበታቸው የሚያቋርጡትን ተማሪዎች ቁጥር መቀነስ መቻል ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ የወንድ እና የሴት ተማሪዎች ቁጥር በመጠኑም ቢሆን እየተቀራረበ የመጣ ቢሆንም እኩል ለእኩል ለማድረግ ገና ብዙ ሥራ ይቀረናል፡፡ በሀገራችን በአጠቃላይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጀመሩ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ፡፡
8. አሁን በሥራ ላይ የሚገኙት የትምርት አገልግሎት ተቋማት (ትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች) በአብዛኛው በጥሩ ሁኔታ ላይ አይደሉም፡፡ በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎት እንዲሰጡ እዲሻሻሉና የትምህርት ጥራት አምጪ (የላብራቶሪ፣ የቤተ - መጻሕፍት ፣ ወርክሾፕ፣ የፔዳ ጎጂ፣ አይ ሲቲ ማዕከላት) ግብዓቶች ዘመናዊ ማድረግ ለትምህርት ጥራትና አግባብነት አስተዋጽዖ ከፍተኛ ስለሆነ ትኩረት መስጠት ያሻል፡፡
9. ዓለም የደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ደረጃ በማገናዘብ የቴክኒክና ሙያ ፕሮግራም ተግባራዊነት በማቀድ የሚሰጠው ትምህርት አግባብነቱ ከተገላጋይ መሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ዘርፎች ማለትም ከጤና፣ ግብርና፣ የምግብ አቅርቦት፣ የኃይል ምንጭ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ከውሃ አቅርቦትና ኢንዱስትሪ ጋር በማስተሳሰር እና በማቀናጀት ለሀገራችን ልማትና ዕድገት ቁልፍ ሚና እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
10. ከመደበኛው ትምህርት ጎን ለጎን ተግባራዊ የሆነ የጎልማሶች ትምህርት በሀገሪቱ ተደራሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ አሁን የሚገኘው 60% መሃይምነትን (ማንበብ/መጻፍ እና ስሌት አለመቻል) በፍጥነት እንዲቀንስ እና ሀገራችን ያልተማሩ ዜጎች የሌሉባት ለማድረግ መሥራት ዓላማው ያደረገ ረጅም ጉዞ ይጠበቃል፡፡

በመጨረሻም የዚህች አጭር ጽሑፍ መልዕክት የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት ካለበት ቀውስ ይወጣ ዘንድ የለውጡን ጉዞ በጥንቃቄ እና በጋራ በማቀድ ዘላቂና አስተማማኝ የትምህርት ሥርዓት መገንባት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን ለመግለጽና ኢዜማም የትምህርት ፖሊሲ አቅጣጫውን በመቅረጽ ላይ እንደሚገኝ ለማስገንዘብ ነው፡፡

# ም/መሪው በ8 የአሜሪካ ከተሞች ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመክሩ ይሆናል፡፡



መስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምክትል መሪ አንዱዓለም አራጌ የፓርቲውን ዓላማ እና የታቀዱ እንቅስቃሴዎችን ለማስተዋወቅ በያዝነው ሳምንት መጨረሻ ወደ ሰሜን አሜሪካ እንደሚያቀኑ ታወቀ።

ምክትል መሪው ወደ ሰሜን አሜሪካ በሚያደርጉት ጉዞዋቸው በዋሽንግተን ዲሲ፣ አትላንታ፣ ሳን ሆዜ፣ ላስ ቬጋስ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ሲያትል፣ ዴንቨር እና ዳላስ ከተማ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር ተገናኝተው የሚወያዩ ይሆናል፡፡

ከዚህ ቀደም የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ፣ ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ፣ የፓርላማ አባላት እጩ ተወካይ ግርማ ሰይፉ እና የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ናትናኤል ፈለቀ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ ግብ እና አላማ ለማስተዋወቅ ወደ ሰሜን አሜሪካ ተጉዘው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

# በኢዜማ ፕሮግራም፣ ደንብና ፍልስፍና ላይ ስልጠና ተሰጠ፡፡

መስከረም 15 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)






የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኤዜማ) ቅዳሜ መስከረም 10 ቀን 2012 ዓ.ም እና እሁድ መስከረም 11 ቀን 2012 ዓ.ም ለአባላቶቹ ስልጠና ሰጠ፡፡

ስልጠናው የተዘጋጀው በኢዜማ ሥር ባለው የስልጠና ዲፓርትመንት ሲሆን ቅዳሜ መስከረም 10 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠው ስልጠና በኢዜማ ፕሮግራምና ፍልስፋና ላይ ያተኮረ የነበረ ሲሆን በእለቱም በስልጠናው ተካፋይ ለነበሩ አባላትና አመራሮች የኢዜማ የስትራቴጂክ እቅድ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ስልጠናው እሁድ መስከረም 11 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን የእሁዱ ስልጠና በኢዜማ ደንብ ላይ የሚያጠነጥን ነበር፡፡ ስልጠናውን ያዘጋጀውና በኢዜማ ሥር የሚገኘው የስልጠና ዲፓርትመንት የስልጠናው አላማ የፓርቲው አባላትና አመራሮች አቅም ማጎልበት መሆኑን ለዜጎች መድረክ ገልጿል፡ ፡ በቀጣይነትም የአባላትን አቅም ለማጎልበት መሰል ስልጠናዎች እንደሚዘጋጁ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የስልጠና ዲፓርትመንቱ በዋና ፅ/ ቤት ሥር የሚገኝ መሆኑንና በሥሩም 5 አባላት ያሉት ሲሆን አንድ ሊቀመንበር፣ አንድ ፀሐፊና 3 አባላት የተዋቀረ ነው፡፡



# ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች

# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደርሳችሁ።